ያልተዘመረላቸው ጀግኒቶቻችን

ፈረንጆቹ የካቲትን የጥቁሮች ታሪክ ወር መጋቢትን ደግሞ የጥቁር ሴቶች የታሪክ ወር በማለት ይዘክሩታል። አድዋ በሚከበርበት የጥቁር ሴቶች ታሪክ ወር ለአገራችን መቆም ምሶሶ የነበሩ ያልተዘመረላቸው ሴቶቻችንን እንዘክራለን። መላው አፍሪካዊያን በባርነት ረግረግ በሚዳክሩበት ወቅት፤ ከወደ ጦቢያ ህልም የሚመስል ወሬ ተሰማ፡፡ የአድዋ ድል! የአድዋ ጦርነት ወንድ ሴት አልለየም። ከንጉስ እስከ ባለሟል፣ ከገበሬ እስከ ጦረኛ፣ በጉልበት አዳሪ እስከ አዝማሪ ያልተሳተፈ ኢትዮጵያዊ የለም።

በአድዋ ጦርነት በሴቶች ተሳትፎ የአንበሳውን ድርሻ የምትወስደው እቴጌ ጣይቱ ብጡል፣ ሴት ፊታውራሪዎች፣ የዘማቾች ሚስቶች እናቶች፣ በግጥም የወንዶቹን ሞራልና ወኔ አቀባይ አዝማሪዎች ብዙ ያልተዘመረላቸው የአድዋ ድል ባለታሪኮች አሉ። ዛሬ በትንሹ የሴቶቹን የጀግንነት ታሪክ እንይ።

ከእቴጌ ጣይቱ እንጀምር

የእቴጌ ጣይቱ የአድዋ ገድል የሚጀምረው ለአድዋ ጦርነት መነሻ ከሆነው ከውጫሌ ስምምነት ነው፡፡

ኮንት አንቶኔሊ የውጫሌ ውል እርሱ እንደፈለገው እንደማይሆን እና 17ኛው አንቀፅ እንደተሰረዘ በሰማ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ እና አጤ ምኒልክ በተቀመጡበት እልፍኝ ገብቶ የ 17 ተኛዉ ክፍል ተሰርዞአል ተብሎ ተፃፈ በማለት አጤ ሚኒልክን ይጠይቃል፣ አጤ ሚኒልክም ሁለታችን አንተና እኔ ተነጋግረን አንተ ወደህና ፈቅደህ የተፃፈ ቃል ነዉ ሌላ አልታከለበትም ባስተርጐሚህ የተናገርከዉ ነዉ አሉት። ከዛ ኮንት አንቶኔሊ እንዳልተሳካለት አዉቆ የዉሉን ወረቀት ቀዳደደውና ጦርነቱ እንደማይቀር ተናግሮ ከልፍኝ እየወጣ እያለ እቴጌ ጣይቱ ከት ብለዉ በመሳቅ “ የዛሬ ሳምንት አድርገዉ በዚህ የሚደነግጥ የለም፣ ሂድ የፎከርክበትን አድርግ እኛም የመጣዉን እናነሳዋለን። እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰዉ ከዚህ የሌለ አይምሰልህ የገዛ ደሙን ገብሮ፣ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጥ ነዉ እንጅ ሞት አይደለም አሁንም ሂድ አይምሽብህ የፎከርክበትን በፈቀደህ ጊዜ አድርገዉ እኛም ከዚሁ እንቆይሀለን”

“ያንተ ፍላጐት ኢትዮጵያ በሌላ መንግስት ፊት የኢጣሊያ ጥገኛ መሆኗን ለማሳወቅ ነው። ነገር ግን ይህን የመሰለው የምኞት ሃሳብ አይሞከርም!! **እኔ ራሴ ሴት ነኝ። ጦርነት አልፈልግም። ነገር ግን ይህን ውል ብሎ ከመቀበል ጦርነትን እመርጣለሁ!**” በማለት ፈፅሞ በኢትዮጵያ ሉአላዊነት እንደማይደራደሩ መናገራቸውን ጳውሎስ ኞኞ አጤ ምኒልክ በሚለው መፅሃፍ አስፍረዋል፡፡

ጣይቱ አንቶኔሊን “የኔ ሴትነትና ያንተም ወንድነት የሚለየው እዚህ እንዳሻህ በተፈራገጥክበት የምኒልክ እልፍኝ ሳይሆን እዚያው ጦር ሜዳ ላይ ነው!!!…ሂድ!…ሂድ መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ!” ብለው ከሸኙ በሁዋላ የጉያ ጠላትን መመንጠር መጀመራቸውን ድርሳናት ያወሳሉ። ከፉ ቀን በመጣ ቁጥር ኢትዮጵያችን ጉድ እንዳየች ነው።

ጣይቱ ነፍስያቸው ነግራቸዋለች። ባንዳን ከሀዲን ጉያ ይዞ እድገትና ጦርነት የፈናጅራ መሆኑ፤ የእሳት ልጅ አመዶቹ፣ የቤተመንግስት ማደጎዎቹ የጣሊያን ደጋፊዎቹ አፈ-ቄሳር አፈወርቅ ገብረኢየሱስ፣ ልጅ ጉግሳ ዳርጌና ልጅ ቅጣው ዛማኑኤል ከጉደኞቹ ባንዳዎች መሃል ነበሩ።

በንጉስ ሚኒሊክ እገዛ ወደስዊዘርላንድ እንዲማሩ የተላኩት እኚሁ የእቴጌ ዘመዶች እዚሁ ኢትዮጵያ የጀመራቸው ባንዳነት ከተላኩበት ከስዊዘርላንድ ወደ ጣሊያን አስኮበለላቸው፣ ከጣሊያን ጋር ሆኖ ኢትዮጵያን ለመውጋት። የመኮብለላቸውእና ለጣሊያን ማደራቸው ወሬው ኢትዮጵያ ሲሰማ የምኒልክን አላውቅም የጣይቱን ግን በቁጣ ነደዱ። እንደውም ሲተረክ

አፈወርቅ ጣሊያን ሄዶም አላረፈም። ጣይቱን ዘመዴ ናት ብሎ አንጀት ሊያባባ የክርስቶስን ስቅለት የሚያሳይ ስእል ቢልክላቸው ጣይቱ ቅጥል ንድድ ከማለታቸው ብዛት “ይስቀልህ! ይ.....ስቀልህ! ስ..ቅ..ል ያድርግህ” አሉ ይባላል።

የክተት አዋጁ

የጦርነት አይቀሬነት እና የጣሊያን ጦር ቅብጥብጥነት እያየለ ትግራይን በመውረሩ ኢትዮጵያም ለፍልሚያ ተዘጋጀች። ዝነኛው የአፄ ምኒልክ የክተት አዋጅም ነጋሪት እየተጎሰመ ተለፈፈ።

“እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ፡፡ እኔም እስካሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ፡፡ ከእንግዲህ ግን ብሞትም ሞት የሁሉም ነውና ለእኔ ሞት አላዝንም፡፡ ደግሞ እግዚአብሔር አሳፍሮኝ አያውቅም፡፡ ከእንግዲህም ያሳፍረኛል ብዬ አልጠረጥረውም፡፡ አሁንም ሀገር የሚያጠፋ፣ ኃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሔር የወሰነልንን ባሕር አልፎ መጥቷል፡፡ እኔም የሀገሬን ከብት ማለቅ፣ የሰውን መድከም አይቼ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር፡፡ አሁን ግን በእግዚአብሔር ረዳትነት ሀገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፡፡ የሀገሬ ሰው ከአሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም፡፡ አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም፡፡ ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ፣ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለምሽትህ፣ ለኃይማኖትህ ስትል በሐዘን እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ፣ አልተውህም፡፡ ማርያምን!! ለዚህ አማላጅ የለኝም፡፡ ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከ ጥቅምት እኩሌታው ድረስ ወረ-ኢሉ ከተህ ላግኝህ”

በጦርነት መሃል

ምኒልክ አዋጅ አስነግረው ካዲስ አበባ ወደ ትግራይ በእግር ጉዞ ጀምረዋል። ቀድመው የደረሱት እና ቦታው የነበሩ መኳንንት ንጉሱ ሳይደርሱ የአምባላጌውን የጣሊያን ጦር ደርማምሰው መቀሌ ደርሰዋል። የአምባላጌው ድል ያጀገናቸው አባቶቻችን በራስ መኮንን መሪነት የመቀሌውን የጣሊያን ጦር ምኒልክ ከመድረሳቸው በፊት ለመምታት ያደረጉት ተደጋጋሚ ጥረት ብዙ የሰው ሕይወት አስቀጠፈ። ዋና ጦር መቀሌ ደርሶ ምክር ሲቀመጡ ጣይቱ ራስ መኮንንን ምን ነካህ እንዴት ይህንን ሁሉ ሰው ታስጨርሳለህ ብለው ገሰጡ።

ታዲያ የመቀሌ የጣሊያን ጦር ምሽግ ብርታት እቴጌይቱን ለፈጣን መላ ጋበዘ። ለአጃቢ ወታደሮቻቸው የመስዋዕትነት ግብዣ አቀረቡ ሕይወታችሁን ስጡኝ። ለምታልፉ ተዝካራችሁን አወጣለሁ የሙት ልጆቻችሁን አሳድጋለሁ!። ግብዣውን ተቀብለው ከ600 እስከ 900 ወታደሮች ቀርበው ተሰናብተው ሄዱ። ከዛ ያለፈው ታሪክ ነው። እነዚያ ወታደሮች የመቀሌውን የጣሊያን ጦር የመጠጥ ምንጭ ያዙ። ጣሊያን የሆዱ ነገር አሸነፈውና የመቀሌው ምሽጉ ባስደናቂ ሁኔታ ተሰበረ።

ሌላው በአድዋ ጦርነት ወቅት ሴቶች ከፍተኛ የሞራል ግንባታ እና የስነ-ልቦና ጦርነት ስራ ሰርተዋል፡፡ ሰራዊቱ ወኔው እንዳይላላ በግጥምና በቋጭት በማነቃቃት ረገድ ሴቶች የማይተካ ሚና እንደተጫወቱ ይነገራል፡፡

ይህንን በተመለከተም ታዋቂው የታሪክ ጸሐፊ ተክለፃድቅ መኩሪያ በድርሳናቸው እንደገለጹት፣ በጊዜው እንደነበረው ልማድ ጣይቱ ወይዛዝርቱና ደንገጡሮቻቸው ዓይነ-ርግብ አድርገው ነው ወደ ትግራይ ጉዞ ያደረጉት። የፊት መሸፈኛው ማንነትን ስለማያሳይ የተገለጠ እለት ድንቅነትም አለው። ከአድዋው የጣሊያን ጦር መሃል አሁን በዘመናችን ኮማንዶ እንደምንላቸው በሻለቆች የሚመሩ ልዩ ሐይል አጥፍቶ ጠፊዎች ነበሩበት። እነዚህ የጣሊያን አጥፍቶ ጠፊ ሐይላት በአድዋ ኮረብቶች የፈሰሰውን የኢትዮጵያን ጦር መሃሉን ለመምታት ያደረጉት ጥረት ተሳክቶላቸው በዚያ ግንባር የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ነቅሎ መሸሽ ጀመረ። ሽሽት የጀመረውን የሚያቆመው ሀይልም ያለ አልመስል አለ። ያኔ ነበር መለኛዋ

ጣይቱ ወይዛዝርቱ ከነደንገጡሮቻቸው የፊት መሸፈኛቸውን ገልጠው ከጦሩ ጀርባ ብቅ ያሉት። ንግስትን በዓይን የማየት፣ የንግስትነት ግርማቸውን የማየት መግነጢሳዊ አድናቆት። ለሚሸሸው ጦር **ንጉስህ ሳይመለሱ እኔን ሴቷን አልፈህ የት ልትገባ ምን አገር አለህ?** ነበረ የጣይቱ ንግግር። የነጣይቱ መገለጥ እና ንግግር የጦሩን ሽሽት ከማስቆሙም ባሻገር ጦሩ ተመልሶ ወደ ውጊያ እንዲገባና የጣሊያንን አጥፍቶ ጠፊ ሐይላት ለወሬ ነጋሪ እንዳይተርፍ አድርጎ ቀጥቷቸዋል።

እቴጌይቱ በአምስቱ ወራት የእግር ጉዞ ገበሬው ሰራዊት እንዳይደክም በየጊዜው ግብር እየጣሉ ከበር መልስ ያበሉ ነበር። የጦርነቱ ለት ታዲያ የጣልያንን ሰራዊት ዘመናዊ ትጥቅ ያየ የተወሰነው ጦር ለመሸሽ ካጀለው። ጣይቱም ብቅ ብለው እንዴ እንዴት ግብሬን በልተህ ጠጄን ጠጥተህ ልትሮጥ? በማለት መልሰው ወደጦርነቱ እንዲገቡ አድርገዋቸዋል።

ይህ ጦርነት ከክተቱ እስከ ድሉ አምስት ወር ከነመልሱ ደግሞ ስምንት ዘጠኝ ወር የፈጀ ነው። የስምንት ወር የእግር ጉዞ፣ የስምንት ወር የመንገድ መኘታ፣ ዝናቡ ጸሃዩ ውርጩ ቁሩ ብርዱ ሀሩሩ፣ የዚሁ ሁሉ ሰውስ ስንቅ እንዴት ነበር?

የጓዳ ጀግኖቻችን

ስለ አድዋ ሲነሳ ሊቆቻችን ባዳራሹና በጦር ሜዳ የተከሰተዉን ሲተነትኑ የእልፍኙ ጀብዱ ብዙ አይወሳም:: እስቲ አስቡት እናቶቻችን ከ 600 ኪ.ሜ በማያንስ ርቀት ዉስጥ በየጣብያዉ ተንቀሳቃሽ ማድቤት እየገነቡ 100 ሺ ሰራዊት ለሁለት ወር ያህል በየቀኑ መመገብ ችለዋል:: ያንን ሁሉ ሠራዊት በዚህ አይነት ቀጥ አድርጎ መመገብ መቻልን የመሰለ ምን ጀብድ ይገኛል!!! ሴቶች ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ለምኔ ብለዉ በምድጃ መለብለብ ነበረባቸዉ:: እንዳለመታደል ሁኖ የምጣድ ጭስ የባሩድ ጭስን ያክል ከያኒዎችን ስለማይስብ አልተነገረላቸውም። ላገር ደም ማፍሰስ እንጂ ላገር ላብ ማፍሰስ አገልግሎት መሆኑን ማን በነገራቸው?

በርግጥ የአድዋዎቹ ባለገድሎች በቤትና በማዕድቤት ብቻ አልተወሰኑም። በውጭ ጀብዱም ቢሆን በጦር መሪነት ደረጃ የውጭ ግንኙነት ቀያሿና ከ17 ሺህ በላይ ጦር መሪዋ እቴጌ ጣይቱን ጨምሮ ከሴት ፈታውራሪዎች መካከልም የሶስት ሺህ ጦር መሪ የጣይቱ እህት ወይዘሮ አዛለች ብጡል፣ የከምባታ ጦር መሪዋ ወይዘሮ ልክየለሽ በየነ፣ የፊታውራሪ ገበየሁ እህት እቴነሽ ጉርሙ፣ የሶስት ሺህ ጦር መሪዋ ወይዘሮ አበበች ጨርቆሴ፣ የደጃዝማች ባልቻ ሳፎ እህት ልጅ ወይዘሮ ድርቤ ጋዲሳና ወይዘሮ አመልማል ገብሬን ለአብነት ይጠቀሳሉ።

በታሪክ የምትወሳው የየላስታ እና የዋግ የጦር መሪው የጊድን ገብሬ እህትም ነበረች። በጦርነቱ ጥይት በቀሚሥ ጫፍ እየቆረጠች ስታቀብል አብራ ተሰውታለች። ለዚህም ታዲያ የሚከተለው ተገጥሞላታል።

የጊድን እኅት ምጥን ወይዘሮ

ጥይት አቀባይ እንዳመልማሎ

አዝማሪ ጣዲቄ

በአድዋ ጦርነት ከዘማቹ አጠገብ በመሆን ወኔ ቀስቃሽ ግጥሞችን በማቅረብ ከሚታወቁት ከእነ እልፎ ወናፎ፣ምድር አረበበች፣ አስማማው መሀለኩል ግንባርቀደም ሆና የምትታወቀው አዝማሪ ጣዲቄ ናት:: አዝማሪ ጣዲቄ ዘማቹን በማነቃቃት በኩል ማንም የሚበልጣት አልነበረም:: ጠየም ሰለምለም ቆጣ የምትለው አዝማሪ ጣዲቄ በአድዋ ጦርነት የጀግኖችን ልብ በመቀስቀስ በኩል የፈፀመችው ተግባር በርካታ ነው:: የሚያውቋት ጣዲቄ ሲሏት እሷ ምን አውቄ ትላቸዋለች::

አፄ ምኒሊክ ከሴት አዝማሪዎች ሁሉ አዝማሪ ጣዲቄን ያቀርቧት ነበር። በኋላም ጣዲቄ በአድዋ ጦርነት ላደረገችው አስተዋጽኦ ከምኒልክ እጅ ሽልማትና ሳታገባ የወይዘሮነት ማዕረግ ተቀዳጅታለች።

አዝማሪ ጣዲቄ ጀግናውን “**አንተ ካለ በሀገሩ ሰላም ነው መንደሩ”** እያለች ታሞጋግስ ነበር። ፈሪውን ደግሞ እንዲበረታ እያደረገች አንፀባራቂ ገድል ፈጽማለች። አዝማሪ ጣዲቄ ውሎና አዳሯ ከወንዶች ጋር ነበር። በመቀሌ ውጊያ ፣ ጣልያኖች ለጊዜ መግደያ እርቅ ሲያስቡ ጣዲቄ ርቁን የይስሙላና የጊዜ መግዣ መሆኑን በመገንዘብ እንዲህ ስትል ትችት አቅርባለች ።

" አውድማው ይለቅለቅ ፣ በሮችም አይራቁ

ቀድሞም ያልሆነ ነው ፣ ውትፍትፍ ነው እርቁ "

ያለችው ሳይቀር የአድዋ ጦርነት እርግጥ ሆነ። ጣዲቄ በዓድዋው ጦርነት ወቅት በየዓውደ ውጊያው እና በየጦር ሰፈሩ በመገኘት ካበረከተቻቸው ዘመን ተሻጋሪ ግጥሞች መካከል የሚከተለውን ብዬ ላብቃ።

1. ማን እንደ አንተ አርጎታል

የእርሳሱን ጉትቻ

የዳኘው አሽከር አባ ነፍሶ ባልቻ።

2. ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ፤

መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ።

3. ዓድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው፤

ገበየሁ በሞቱ ግባና ቀድሰው።

እኔ የዘመኔ ጣይቱ ነኝ፣ እናንተስ?